የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 5
ADDIS ABABA 25th December, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፯/፪ሺ፩ ዓ.ም

በአፍሪካ አገራት መካከል አፍሪካዊ ቴክኒክ ትብብር መርሀ-ግብር መመስረቻ ኮንቬንሽንን አዋጅ …ገጽ ፬ሺ፫፻፷፱

CONTENTS

**Proclamation No. 607/2008**

The Inter-African Convention Establishing an African Technical Co-operation Programme Ratification Proclamation Page 4369

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፯/፪ሺ፩

### በአፍሪካ አገራት መካከል አፍሪካዊ የቴክኒክ ትብብር መርሀ-ግብር መመስረቻ ኮንቬንሽንን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በአፍሪካ አገራት መካከል አፍሪካዊ የቴክኒክ ትብብር መርሀ-ግብርን የሚመሠርተው ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ. ኦገስት ፩ ቀን ፲፱፻፸፭ በካምፓላ /ዑጋንዳ/ በተካሄደው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባኤ የፀደቀ በመሆኑ፤

አገራችን ይህንን ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፰ ቀን ፪ሺ፯ የፈረመች በመሆኑ፤

ይህንኑ ኮንቬሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በአፍሪካ አገራት መካከል አፍሪካዊ የቴክኒክ ትብብር መርሀ-ግብር መመስረቻ ኮን ቬንሽንን ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፯/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 607/2008.

### PROCLAMATION TO RATIFY THE INTER-AFRICAN CONVENTION ESTABLISHING AN AFRICAN TECHNICAL CO-OPERATION PROGRAMME

**WHEREAS,** the Ordinary Session of the Organization of African Unity Heads of States and Governments meeting held in Kampala (Uganda) on 1st August, 1975, adopted the Inter-African Convention Establishing an African Technical Co-operation Programme;

**WHEREAS,** Ethiopia has signed the Convention on 28 December 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Convention at its session held on 16th day of December, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "The Inter-African Convention Establishing an African Technical Co-operation Programme Ratification Proclamation No. 607/2008."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. የኮንቬንሽኑ መፅደቅ

እ.ኤ.አ. ኦገስት ፩ ቀን ፲፱፻፸፭ በካምፓላ /ዑጋንዳ/ የፀደቀው በአፍሪካ አገራት መካከል የቴክኒክ መርሀ-ግብርን የሚመሠርተው ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ሥልጣን

የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ኮንቬንሽኑ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Convention

The Inter-African Convention Establishing an African Technical Co-operation Programme which was adopted on 1st day of August 1975 is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Capacity Building

The Ministry of Capacity Building is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Convention.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of December, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**